የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት

የአፋር ክልል ነጋሪት ጋዜጣ

AFAR REGION NEGARIT GAZETA

OF THE AFAR NATIONAL REGIONAL STATE

ሁለተኛዓመትቁጥር7 አይሳኢታሐምሌ1ቀን091	በአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት ጠባቂነት	2nd Year No. 7 AYSAITA-8th July,2001

ማውጫ

የአፋር ዘላቂ የአካባቢ ተሀድሶና የእርሻ ልማት የወረዳ ግብርናና የተቀናጀ የገጠር ልማት አገልግሎት ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅ _____ ገጽ 1

የአፋር ዘላቂ የአካባቢ ተሀድሶና የእርሻ ልማት የወረዳ ግብርናና የተቀናጀ የገጠር ልማት አገልግሎት ኮሚሽን ለማቋቋም የወጣ አዋጅ

በአፋር ክልል ከፍተኛ የአካባቢ መራቆት የተባባሰ መሆኑንና ህብረተሰቡ ለአስከፊ የገጠር ልማት አገልግሎት እጥረት የተጋለጠ በሆኑ በክልሉ የአካባቢ ተሀድሶ በመፍጠርና ወረዳን ያማከለ የተቀናጀ የገጠር ልማት አገልግሎት በመዘርጋት የሕዝቡን የኑሮ ደረጃ ማሻሻል አስፈላጊ በመሆኑ፣

የክልሉ የህብረተሰብ በምግብ ራሱን እንዲችልና በክልሉ ብልፅግናን ለማፋጠን በኢኮኖሚ መስኮች መካከል ያለውን ትስስር በየወረዳው ማጠናከር በማስፈለጉ ክልሉ ካለበት ኋላቀር የእድገት ደረጃ ለማላቀቅ እና ንብረተሰቡ በዋነኛነት የማፈልጋቸውን የልማት ሥራዎች ለማስፋፋት ክልሉ ተጨባጭ ሁኔታ ጋር ኘሮግራም የተገናዘበ መከተል በማስፈለጉ የአፋር የግብርናና የተፈጥሮ ሀብት ከተጋለጠበት ከፍተኛ ብክነትና ጥፋት አድኖ ማልማትና ጥቅም ላይ ማዋል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘት የገጠሩን ህብረተሰብ ገቢውን ማሳደግ የሥራ እድልን መፍጠር የቴክኒክ ሙያና የሥራ እውቀቶችን ማስፋፋት እንዲሁም ከብት አርቢውን ህብረተሰብ ወደ ተሰባሰበና ቋሚ የኑሮ ሁኔታ እንዲመጣ ማድረግ መርዳት አስፈላጊ በመሆኑ የእርሻ ምርት ለማሳደግና በምግብ ራስን ለመቻል አስተማማኝ የአካባቢ ተሀድሶ ዘዴዎችን መጠቀም አስፈላጊ ስለሆነ የግብርና ምርትና ምርታመነትን ለማሳደግ በእርሻ እና በእንስሳት እርባታ ከገጠር ልማት ጋር ማቀናጀት አስፈላጊ በመሆኑ ይህንን ለመፈፀም ራሱን የቻለና ከገጠር ከብት አርቢ ህብረተሰብ ጋር የሚሠራ የማኔጀመንት አካል ማቋቋም አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ በአፋር ብሔራዊ ክልል ሕገ መንግስት አንቀጽ 7 ቁጥር 2-2 መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

ጠቅላላ

1. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ የአፋር ዘላቂ የአካባቢ ተሀድሶና እርሻ ልማት በወረዳ ግብርና የተቀናጀ የገጠር ልማት አገልግሎት ኮሚሽን ለማቋቋም የወጣ አዋጅ ቁጥር 8/09□□1 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. ትርጓሜ

የቃሉን አገባብ ሌላ ትርጉም ካልተሰጠው በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ

1. ኮሚሽን ማለት የአፍሪካ ኢኮኖሚ ኮሚሽን ወይም አንድ አግባብ የአፋር ዘላቂ የአካባቢ ተሀድሶና እርሻ ልማት በወረዳ ግብርና የተቀናጀ የገጠር ልማት ኮሚሽን ማለት ነው።
2. ኘሮግራም ማለት የዘላቂ የአካባቢ ተሀድሶና እርሻ ልማት በወረዳ ግብርና የተቀናጀ የገጠር ልማት ኘሮግራም ማለት ነው።
3. የአገልግሎት ማለት የኮሚሽኑ ኘሮግራም አገልግሎት ማለት ነው።
4. የተቀናጀ የገጠር ልማት ማለት በገጠር የኢኮኖሚ መስኮች መካከል ያለውን ትስስርና ብልፅግና ማለት ነው።
5. ኮሚሽን ማለት የአፋር ክልል የዘላቂ የአካባቢ ተሀድሶና እርሻ ልማት በወረዳ ግብርና የተቀናጀ የገጠር ልማት ኮሚሽን ኮሚሽነር ማለት ነው።
6. ግብርና ሥራ ማለት በግብርና ልማት በአግሮ ኢንዲስትሪ እና በግብርና አገልግሎት መስክ የሚካሄድ ሥራ ነው።

- የግብርናልማትማለትየቋሚናየዓመታዊሰብሎችልማትየእንስሳትናየዓሳሀብትልማትናቀዋጽኦየደንየዱርአራዊትልማትናተዋጽኦነው ።
- የአግሮ ኢንዱስትሪ ማለት ማናቸውም ሰው የራሱን የግብርና ተረፈ ምርትና በተጨማሪ ለተጠቃሚው በሚያመች ዘዴ በፋብሪካው አደረጃጀትም አቀነባብሮ ለማቅረብ የሚያካሂደው የሥራ መስክ ነው።
- ግብርና አገለግሎት ማለት በግብርና ሥራ ለተሠማሩ የአገልግሎት ክፍያ በመቀበል የቴክኒክ አገልግሎት ለመስጠት የሚቋቋም የሥራ መስክ ነው።
- ግብርና አገልግሎት ማለት በግብርና ሥራ ለተሠማሩ የአገልግሎት ክፍያ በመቀበል የቴክኒክ አገልግሎት ለመስጠት የሚቋቋም የሥራ መስክ ነው።

7. የተፈጥሮና የእርሻ ሀብቶች ማለት የአፋርኛ ውሃ ግጦሽ አትክልት እንስሳትና ሌሎች ለገጠር ኑሮ አስፈላጊ የሆኑ የተፈጥሮ እና የእርሻ ሀብቶች ማለት ነው።
8. ተጠቃሚ ማለት ኑሮው በከብት እርባታ በእርሻ ሥራ በሌላ በማንኛውም የግብርና ሥራ ወይም የገጠር ሀብት የተመሠረተና በኮሚሽኑ የመስኖ ኘሮግራም ተጠቃሚ የሆነ ሰው ወይም ቡድን ማለት ነው።
9. ሰው ማለት ማንኛውም የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው።
10. ክልል ማለት የአፋር ብሔራዊ ክልል ማለት ነው።
11. መንግስት ማለት የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ወይም እንደአግባቡ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ መንግስት ማለት ነው።

12. ወረዳ ማለት ማንኛውም በአፋር ብሔራዊ ክልል ውስጥ እውቅና የተሰጠው ወረዳ ማለት ነው።

13. ዘላቂ እርሻ ማለት የተፈጥሮ እና የእርሻ ሀብቶች ሕዝብ በአግባቡ እንዲተዳደር እንዲጠቀምበትና እንዲያሳድገው እያደረገ የሚቀጥለው ትውልድ በተመሳሳይ መንገድ ጠብቆና አሳድጐ መጠቀም ማለት ነው።

14. ኮንፈረንስ ማለት ክልላዊ የተጠቃሚዎች ኮንፈረንሰ ማለት ነው።

15. ቦርድ ማለት በዚህ አዋጅ የተቋቋመ የኮሚሽኑ ቦርድ ማለት ነው።

3. ስለመቋቋም

1. የአፋር ዘላቂ የአካባቢ ተሀድሶና እርሻ ልማት በወረዳ የተቀናጀ የገጠር ልማት ኮሚሽን የህግ ሰውነት ያለውን ራሱን የቻለ የመንግስት መስሪያ ቤት ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል።
2. የኮሚሽኑ ተጠሪነት ለክልሉ ሥራ አስፈፃሚና ለርዕሰ መስተዳድሩ ይሆናል።

4. የኮሚሽኑ ዓላማዎች

1. የመስኖ እርሻ እንዲስፋፋ በማድረግ የምግብ እጥረትን ማቃለል፣
2. በገደብ ተፋሰስ የተፈጥሮ ሀብት ልማትና ጥበቃ እንዲካሄድ ማድረግ፣
3. መሠረታዊ የሆኑ ማህበራዊ አገልግሎቶችን በማቅረብና በማጠናከር በዋነኝነት የገጠሩን ህዝብ የኑሮ ደረጃ ማሻሻል፣
4. የኢኮኖሚ መሠረተ ልማቶችና አገልግሎቶችን በመዘርጋትና በማቅረብ የከብት አርቢው ህብረተሰብ ምርታማነትና የማግኘት አቅም ማሳደግ፣
5. የወረዳው ህብረተሰብን መሠረት ያደረጉ ኘሮጀክቶችን የመለየት፣ የማዘጋጀትና የመተግበር፣ የማስተዳደርና የመንከባከብ ዘይቤን በህብረተሰቡ ውስጥ ማራመድ፣
6. ቀጣይነት ያለው አነስተኛ ብድር ለወረዳ ህብረተሰብ መስጠት የሚችሉ ብድር ሰጭ ድርጅቶችን እንዲፈጥሩና እንዲዳብሩ መርዳት፣
7. ህብረተሰቡን አግዘው የሚሰሩ መሠረታዊ ድርጅቶችንና ማህበረሰቦችን በኘሮጀክት ሥራዎች ቴክኒካዊና የሥራ አመራር ብቃት እንዲዳብሩ መርዳት፣
8. የወረዳ መሠረተ ልማቶች አገልግሎቶች እና አውታሮች ማጐልበት እና ማጠናከር፣
9. ተጠቃሚዎች ኘሮግራም፣ እቅድና በጀት በማውጣትና በመገምገም ችግሮችን በማጤን የግድ ቦታዎችን በመመሪያ በግድብ ሥራዎችና በጥበቃ እንዲሁም መስኖውን በማስተዳደር ተገቢ ተሳትፎ እንዲኖረው ማድረግ፣
10. የህዝብ ተሳትፎ ማጐልበት፣ የአካባቢ ተሀድሶ መፍጠርና የተቀናጀ ልማት በወረዳ ማማከል፣

5. የኮሚሽኑ ስልጣንና ተግባር፣

1. የኮሚሽኑ ሥራዎችን በሚመለከት ሕጐች፣ ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች ያወጣል ሲፀድቅ ሥራ ላይ ያውላል፣
2. የግድቦችንና የመስኖ አውታሮችን ዲዛይን ይሰራል፣ ያንጻል፣
3. ከተጠቃሚዎች ከወረዳ እና ጣቢያ መስተዳድር አካላት ጋር በመተባበር የግድቦችና የመስኖ አውታሮች ደህንነት ይከታተላል፣ እድሳት የሚያስፈልጋቸው እንዲታደሱ ያደርጋል፣

4. በግድቦችና ተፋሰስ ሊሰሩ የሚገባቸውን የአፈርና ውሃ ጥበቃ ዲዛይኖች ለመስራት ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ይተባበራል፣
5. በህዝብና መንግስታዊ ባልሆኑ አካሎች ሊሰሩ የታቀዱ የእርሻ ግድቦች ዲዛይንና ግንባታ ስታንዳርድ ይቆጣጠራል፣
6. የተጠቃሚ ከብት አርቢዎችና ገበሬዎች ምርታማነት እንዲጨምር ግድቦችና የመስኖ አውታሮች እንዲታደሱ እና በአካባቢው ሊደርስ የሚችል ጉዳት ለመቆጣጠር ከተለያዩ መንግስታዊ አካሎች ጋር በመተባበር ይሰራል።
7. ከሚመለከታቸው መንግስታዊ እና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ጋር በመተባበር ህዝቡ ስለግድብና መስኖ በእድሳትና ግንባታ የተጠቃሚዎች ሚና እንዲሁም የውሃ የአርሻ የግጦሽና የመስኖ አጠቃቀም እንዲያውቅ ያደርጋል።
8. አቅም ለመፍጠር የሚያስችሉ ከክልሉ ተጨባጭ ሁኔታ ጋር የሚዛመዱ የሌሎች አገሮች ልመድና ቴክኖሎጂ ያጠናል፣
9. ከተጠቃሚ የክልሉ ከብት አርቢዎችና ገበሬዎች ጋር ስለ ግድብ ቦታ አመራረጥ ግንባታ፣ የመሬትና ውሃና የግጦሽ አጠቃቀም የግድብና መስኖ መዋቅር እድሳትና እንክብካቤ የእዳ አከፋፈልና ለሚፈናቀሉ ገበሬዎችና ለሚሰባሰቡ ከብት አርቢዎች መፍትሄ በሚሰጥ አግባብ ባላቸው ህጐች መመሪያዎችና ደንቦች መሠረት ስምምነት ያደርጋል፣
10. በወረዳ ማዕከልነት ሊከናወኑ መሠረታዊ ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ አገልግሎቶችን ለማቋቋምና ለማጠናከር ህዝባዊ ተሳትፎ ባላቸው ኘሮጀክተር አማካኝነት እርዳታና ብድር መስጠት፣
11. የስልጠና ኘሮግራሞች ለህብረተሰቡ በማዘጋጀት መሠረታዊ የህብረተሰቡ አቅም ማጐልበት፣
12. ሴቶች ማንኛውም የኘሮጀክት ሥራ እንቅስቃሴ እንዲሳተፉ ማበረታታት፣
13. የንብረት ባለቤት መሆን፣
14. ውል ማዋዋል
15. በስም የመክሰስና መከሰስ
16. ዓላማውን ከግቡ ለማድረስ የሚያስፈልጉ ሌሎች ተግባሮችን ማከናወን፣

6. ዋና ጽህፈት ቤት

የኮሚሽኑ ዋና ጽህፈት ቤት ሰመራ ይሆናል፣ ሆኖም ግን እንደአስፈላጊነቱ በሌሎች አካባቢዎች ቅርንጫፍ ሊኖሩት ይችላል።

7. ሕጋዊ ሰውነት፣

ኮሚሽኑ ሕጋዊ ሰውነት ያለው አካል ሆኖ ንብረት የመያዝ ውል የመዋዋል፣ የመክሰስ እንዲሁም ሌሎች አስፈላጊ ተግባሮችን የመፈፀም ስልጣን አለው።

8. የሠራተኛ አስተዳደር፣

የኮሚሽኑ ሠራተኞች ቅጥርና አስተዳደር በአሰሪና ሠራተኛ ህግ መሠረት የሚፈፀም ይሆናል።

9. ኮሚሽኑ፣

1. በክልል ደረጃ የተጠቃሚዎች ኮንፈረንስ
2. ቦርድ
3. በርዕሰ መስተዳድሩ አቅራቢነት በሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ የሚሾም ኮሚሽነርና ምክትል ኮሚሽነር፣
4. ሌሎች አስፈላጊ ሠራተኞች፣

5. የወረዳ ዘላቂ የአካባቢ ተሀድሶና የእርሻ ልማት የተቀናጀ የገጠር ልማት ኮሚቶ፣
6. የግድብ ተጠቃሚዎች ጠቅላላ ጉባኤ፣
7. የግድብ ዘላቂ የአካባቢ ተሀድሶና የእርሻ ልማት ኮሚቴ ይኖሩታል፣

ክፍል ሁለት

ስለኮንፈረንሱ ቦርድ

10. የኮንፈረንሱ አባላት

1. ኮንፈረንሱ በኮሚሽኑ ኘሮግራም ተጠቃሚ የሆኑ ወረዳዎች የሚወክሉ ወንዶችና ሴቶች ወጣት ገበሬዎች አባላት ይኖሩታል፣
2. የኮንፈረንሱ ሊቀመንበር፣ ም/ሊቀመንበርና ፀሐፊ ይኖሩታል፣
3. የአካሎች ብዛት አወካከልና የሥራ ጊዜ በመመሪያ ይወሰናል።

11. የኮንፈረንሱ ተግባርና ያላፊነት፣

1. የኮሚሽኑ ስትራቴጂ፣ ፖሊስና አላማዎችን በተመለከተ ተወያይቶ ሃሳብ ያቀርባል፣
2. የሰው ኃይል ማቴሪያልና ገንዘብ ማሟላትና ማሰማራት በግድብ ሥራ ምክንያት የሚከተል የውሃ፣ የግጦሽና የመሬት አጠቃቀም መዛባት እንዲሁም ሌሎች ከኮሚሽኑ ጋር የተያያዙ ፖለቲካዊና ማህበራዊ ችግሮችን በተመለከተ ተወያያቶ መፍትሔ ያቀርባል።
3. በኮሚሽኑ ዓመታዊ በጀትና እቅድ ተወያያቶ ገምግሞ አስተያየት ይሰጣል።
4. የፈሰሰውን የኢንቨስትመንት እዳ ለመመለስ ጥገናና የሰው ኃይል አጠቃቀም በተመለከተ ተወያያቶ መፍትሔ ሃሳብ ያቅርባል፣ በመንግስት የሚወጡ ሕጐችና ደንቦች ከክልሉ ተጨባጭ ሁኔታ ጋር በሚያጠናክር መልኩ የክልሉ መንግስት የሚያወጣቸው አዋጆችና ደንቦች የማይቃረን የአካባቢ ስሪቶችን ያወጣል፣
5. እንደ አስፈላጊነቱ ከውጭ ኦዲተር በመሰየም የተጠቃሚዎች የኢንቨስትመንት እዳ መመለስ በተመለከተ እንዲመረመር ያደርጋል፣ ሪፖርቱን ተወያይቶ ያፀድቃል።
6. ከአባላት መካከል የቦርድ አባላት ይመርጣሉ።
7. ተጠቃሚዎች በማህበር ተደራጅተው የሚሠሩበትን መንገድ ይጠቁማል፣
8. የቦርዱን ዓመታዊ ሪፖርት ይገመግማል።
9. ወረዳን ያማከለ የተቀናጀ የልማት ጥናትና ምርምር ሰፊ የህብረተሰብ ተሳትፎ ስለሚታቀፍበት መንገድ ይነድፋል።

12. የኮንፈረንሱ ስብሰባ

1. ኮንፈረንሱ በዓማት አንድ ጊዜ ይሰበስባል ሆኖም ግን ቦርድ ጥሪ ሲያደርግ ልዩ ስብሰባ ሊያደርግ ይችላል።
2. ሁለት ሶስተኛ የኮንፈረንሱ አባላት ሲገኝ ምልዓተ ጉባኤ ይሆናል።
3. የኮንፈረንሱ ውሳኔ በአብላጫ ድምጽ ያልፋል ድምጽ እኩል ሲሆን ሰብሳቢ ያለበት ወገን አሸናፊ ይሆናል፣
4. የኮንፈረንሱ አብላጫ ድምጽ ውሳኔ ከነባራዊ እውነታ የሚፃረር እና ከተጨባጭ ሁኔታ ጋር የሚቃረን ከሆነ የአብላጫ ድምጽ ውሳኔው ውድቅ ሆኖ ለጉዳዩ አግባብነት እና ከፍተኛ ብቃት ያላቸው አካላትና ሰዎች ጥልቅ እና ግልጽ

ማብራሪያ በመስጠት የግንዛቤ ማስጨበጥ እና የሶሻል ኢንጂነሪንግ ተግባራት እንዲያከናውኑ ተደርጐ የኮንፈረንሱ አባላት እንደገና ድምጽ እንዲሰጡበት ይደረግና የኮንፈረንሱ አብላጫ ድምጽ እንዲሰጡበት ይደረግና የኮንፈረንሱ አብላጫ ድምጽ የመጨረሻ አሸናፊ ውሳኔ ይሆናል።

13. የቦርድ አባላት

ቦርዱ የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል

1. ርዕሰ መስተዳድር ወይም ተወካይ _____ ሰብሳቢ
2. ኮሚሽነር _____ ምክትል ሰብሳቢ
3. ም/ኮሚሽነር _____ አባል
4. በኮንፈረንሱ የሚወከሉ 12 የተጠቃሚ ተወካዮች _____ አባል
5. የግብርና ቢሮ ኃላፊና የእርሻ ዘዴና ማህበራት ማደራጃ ቡድን መሪ_____ አባል
6. የውሃ ሃብት ቢሮ ኃላፊ _____ አባል
7. የሥራና ከተማ ልማት ማ/ኢ/ኃላፊ _____ አባል
8. የኘላንና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ ኃላፊ _____ አባል
9. የአደጋ መ/ዝ/ሣ/ማ/ጉ/ቢሮ ኃላፊ _____ አባል
10. ንግድ፣ ኢንዱስትሪ፣ ትራንስፖርትና ቱሪዝም ቢሮ ኃላፊ _____ አባል
11. የሥነ ህዝብ ጽ/ቤት ኃላፊ _____ አባል
12. የማስታወቂያና የህዝብ ግንኙነት ጽ/ቤት ኃላፊ _____ አባል
13. የሴቶች ጉዳይ ጽ/ቤት ኃላፊ ወይም ተወካይ _____ አባል
14. የተጠቃሚ ወረዳ የከብት አርቢና የገበሬ ማህበራት ተወካይ _____ አባላት
15. የተጠቃሚ ወረዳ የህብረተሰብ ተወካይ _____ አባላት
16. በክልሉ መንግስት የሚወከሉ 3 የሥራ አስፈፃሚዎች _____ አባላት
17. የምክር ቤቱ ዋና ፀሐፊ /የሚወከል ፀሐፊ _____ ፀሐፊና አባል

14. የቦርዱ ስልጣንና ተግባር

1. የኮሚሽኑ ስትራቴጅ፣ ፖሊሲዎች ህጐችና አሠራሮች ቀርጾ ለአፋር ብሔራዊ መንግስት ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ያቀርባል፣
2. የኮሚሽኑ ዓመታዊ እቅድና በጀት ለአፋር ክልል ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴና ለኮንፈረንሱ ያቀርባል አመታዊ በጀትና የሥራ ኘሮግራም ያፀድቃል፣
3. የክልሉ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴና ኮንፈረንሱ የሚሰጡት ውሳኔዎችና አስተያየቶች ይፈፅማል፣ የሁለቱም ውሳኔዎችና አስተያየቶች በሚቃረኑበት ጊዜ የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴው ውሳኔ ተፈፃሚ ይሆናል፣
4. በዚህ አዋጅና በክልሉ መንግስት በሚሰጠው መመሪያ መሠረት የኮሚሽኑ መዋቅርና ቅርጽ የሠራተኛ አስተዳደር የግድብና የመስኖ ስርዓት ስታንዳርድ መመሪያዎች ያወጣል፣
5. የኢንቨስትመንት እዳ መመለስን በሚመለከት የአፈፃፀም መመሪያዎች ያወጣል፣

6. የቦርዱ ተጠሪነት ለክልል ሥራ አስፈፃሚና ለርዕሰ መስተዳደር ይሆናል፣
7. ቦርዱ ከላይ የተጠቀሰው ዝርዝር ሁኔታ ሳይወሰን፣ የኮሚሽኑ አጠቃላይ እንቅስቃሴ በተቀላጠፈና በሰከነ ሁኔታ ሊፈፀም ይችል ዘንድ በማንኛውም ደረጃ ከሚገኙት ተቋማትና መንግስታዊ አካላት ትብብር ያስገኛል፣
8. ኮሚሽኑ በሚመለከቱ ሌሎች የፖሊሲ ጉዳዮች ላይ ውሳኔ ይሰጣል።

15. የቦርድ ስብሰባ

1. ቦርድ በሶስት ወር አንድ ጊዜ ይሰበሰባል ሆኖም ግን ኮሚሽነሩ የአፋር ክልል ርዕሰ መስተዳደር ወይም የቦርዱ ግማሽ አባላት ጥያቄ ሲያቀርቡ ተጨማሪ ስብሰባ ሊያደርግ ይችላል።
2. ሁለት ሶስተኛው የቦርዱ አባላት ሲገኙ ምልዓተ ጉባኤ ይሆናል፣
3. የቦርዱ ውሳኔ በአብላጫ ድምጽ ያልፋል እኩል ሲሆን የሶሻል ኢንጂነሪንግ ይካሄዳል፣ የሶሻል ኢንጂነሪንግ ተካሂዶ እኩል ድምጽ ከሆነ ሰብሳቢ ያለበትን ወገን ውሳኔ ይሆናል፣
4. ቦርዱ የራሱ የውስጥ ደንብና መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፣ ባወጣው የስብሰባ ስነ ሥርዓት ደንብም ይመራል፣
5. ቦርዱ ከሩብ ዓመቱ መደበኛ ስብሰባ ውጭ በሰብሳቢው ጥሪ የቦርዱ አስቸኳይ ስብሰባዎች በማንኛውም ጊዜ ሊደረጉ ይችላሉ።

16. የኮሚሽነሩ ስልጣንና ተግባር

1. ኮሚሽነሩ የኮሚሽኑ የበላይ ሥራ አስፈፃሚ በመሆኑ የኮሚሽኑን ሥራዎች ይመራል፣
2. የኮሚሽኑ ሥራ ኘሮግራምና በጀት ያዘጋጃል ሲፈቀድም በሥራ እንዲውል ያደርጋል፣
3. ኮሚሽነሩ ከሶስተኛ ወገኖች ጋር በሚያደርገው ግንኙነት ኮሚሽኑን ይወክላል፣
4. የቦርዱን የሥራ እንቅስቃሴ በተመለከተ ሪፖርት ያቀርባል፣
5. በቦርዱ የሚሰጡት ሌሎች ተግባሮች ይፈጽማል፣
6. የኮሚሽነሩ ተጠሪነት ለክልሉ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴና ለርዕሰ መስተዳድሩ ይሆናል፣
7. የኮሚሽኑ እንቅስቃሴዎች በክልሉ ውስጥ እነዲሰራጩ ማድረግ፣
8. በአመልካቾች የሚቀርቡ ተዛማጅ ኘሮጀክቶችን መገምገምና ከውሳኔ ሃሳብ ጋር ለቦርዱ ማቅረብ፣
9. በክለሉ የኮሚሽኑ እንቅስቃሴዎች በቃት ለማከናወን አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ስልጣኑን ለኮሚሽኑ የወረዳ ምክር ቤት በውክልና ሊሰጥ ይችላል፣
10. ለክልሉ ኮሚሽን ጽ/ቤት በተፈቀደው በጀት መሠረት ክፍያዎችን ይፈጽማል፣
11. አግባብ ባለው ህግ መሠረት የኮሚሽኑ ሠራተኛ ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፣
12. ቦርዱና በሥራ አስፈፃሚ የሚሰጠው አጠቃላይ መመሪያ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ኮሚሽነሩ የኮሚሽኑ እንቅስቃሴዎች በኮሚሽኑ የአፈፃፀም ሂደት መሠረት በአግባቡ ተግባራዊ ለመሆናቸው ኃላፊ ይሆናል።
13. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 8 ለኮሚሽኑ የተሰጠውን ስልጣንና ተግባር ይፈጽማል።

17. ስለ ምክትል ኮሚሽነር

1. ኮሚሽኑ አንድ ምክትል ኮሚሽነር ይኖረዋል።

2. ኮሚሽነሩ በሌለበት ጊዜ ተተክቶ ይሠራል፣
3. ተጠሪነቱ ለካሚሽነሩ ይሆናል፣
4. በአንቀጽ 16 ለኮሚሽነሩ የተሰጠ ስልጣንና ተግባር በማስፈፀም ረገድ ኮሚሽነሩን ያግዛል፣
5. ምክትል ኮሚሽነሩ የቦርዱ ፀሐፊ ነው።
6. በአጠቃላይ በዚህ አዋጅ ውስጥ የተካተቱት አላማዎች ተግባራዊ ለማድረግ የሚረዱ እንቅስቃሴዎች በኮሚሽኑ መዋቅር መሠረት የሚሰጠውን ስልጣንና ተግባር ይፈፅማል።

18. በወረዳና በግድብ የሚገኙ የኮሚሽኑ አካላት ስለማቋቋም

በወረዳና በግድብ የሚገኙ የኮሚሽኑ አባላት ስለማቋቋም ስልጣንና ተግባር በመመሪያ ይወሰናል።

ክፍል ሶስት

ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

19. የአሠራር ወጥነትን ስለማረጋገጥ

የኮሚሽኑ የአሠራር ወጥነት ለማረጋገጥ የሥራ አፈፃፀም መመሪያው የኮሚሽኑን አጠቃላይ ተግባራትና እንቅስቃሴዎች የሚገዛ ይሆናል።

20. የበጀት ምንጭ

ለኮሚሽኑ ሥራዎች ማስፈፀሚያ የሚሆን በጀት ምንጮች የሚከተሉት ይሆናሉ።

1. በመንግስት ከሚመደቡ በጀት
2. ከሀር ውስጥና አገር ውጭ መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች፣ ማህበረሰብ እና ግለሰቦች በእርዳታ በቦርድና በወዋጮ የሚገኝ ገንዘብ እና ማቶሪያል፣
3. ከክልሉ ወረዳዎች፣ ከክልሎች፣ ከፌዴራሉ መንግስትና ከለጋሽ ድርጅቶች የሚሰጡ መመሪያዎች፣ እቃዎችና የመሳሰሉት ለኮሚሽኑ ተጨማሪ ገቢዎች ሊሆኑ ይችላሉ።
4. በጀቱ የገንዘብ መዋጮዎች ከተደረጉበት የብድርና እርዳታ ስምምነቶች ጋር በተጣጣመ መልኩ ተግባሪዊ ይሆናል።

21. ኦዲት

1. የኮሚሽኑ የሂሳብ መዝገቦችና ገንዘብ ነክ ጉዳዮች

ሀ/ የኮሚሽኑ የሂሳብ መዝገቦችና ገንዘብ ነክ ጉዳዮች በኮሚሽኑ የውስጥ ኦዲተር በየጊዜው ይመረምራል፣

ለ/ የኮሚሽኑ የሂሳብ መዝገቦችና ገንዘብ ነክ ጉዳዮች ቦርዱ በሚሠይመው ብቃት ያለው የውጭ ኦዲተር ይመረምራል፣

2. የክልሉ መንግስት ኦዲተር በማንኛውም ጊዜ የኮሚሽኑ የመንግስታዊ በጀት አጠቃቀም ሊመረምር ይችላል።

22. የባንክ ሂሳብ

1. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 20 ቁጥር 1 እና 2 የተጠቀሰው መወጮ በኮሚሽኑ ስም በባንክ ተቀማጭ ይሆናል።
2. ኮሚሽኑ የሚከተሉት የባንክ ሂሳቦች ይኖሩታል፡

ሀ/ የውጭ ምንዛሬ ሂሳብ፣ ከውጭ እርዳታና ብድር ሰጪዎች ለሚገኘው ገንዘብ

ለ/ የብር /የአገር ውስጥ ገንዘብ/ሂባራ

3. የኮሚሽኑ የባንክ ሂሳብ በኮሚሽነሩ አና የኮሚሽኑ የፋይናንስ መመሪያ ኃላፊ በአንድነት ይንቀሳቀሳል።

23. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

እስማኤል አሊ ሲሮ

የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት

ርዕስ መስተዳድር